# የኢህአዴግ የምርጫ ሥነ-ምግባር መመሪያ

## መግቢያ

ኢህአዴግ የአገራችን ህልውና ቁልፍ ጉዳዮች የሆኑት ልማት፣ ዴሞክራሲና ሰላም እንዲረጋገጡ በፅናት የሚታገል ድርጅት ነው። እነኚህ ሶስት መሰረታዊ ጉዳዮች አንዱ ከሌላው ሳይነጠል በተሳሰረ አኳኋን ሊገነቡ እንደሚገባቸው ኢህአዴግ አበክሮ ያምናል። ከዚህ በመነሳትም ለተግባራዊነታቸው በሁሉም መስክ ግንባር ቀደም ሚና ሲጫወት ቆይቷል፤ አሁንም በመጫወት ላይ ይገኛል። አገራችን የተያያዘችውን የለውጥ ጉዞ ለማጠናከር ለዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታ ብቁ ትኩረት መስጠት ያስፈልጋል። እዚህም ላይ ኢህአዴግ ግንባር ቀደም ሚና መጫወት ይጠበቅበታል።

ኢህአዴግ ዴሞክራሲያዊ ሥርአት በመገንባት ረገድ እንዲጫወት የሚጠበቅበት ሚና በተወሰኑ ተግባራት ብቻ የታጠረ አይሆንም፤ በሁሉም መስኮች ግንባር ቀደም ሆኖ መገኘትን ይጠይቃል። በአገራችን ዴሞክራሲያዊ ስርአት ከመገንባት አኳያ እጅግ ተፈላጊ ከሆኑት ተግባራት አንዱ ደግሞ ምርጫ ነው። በመሆኑም በአገራችን የሚካሄዱ ምርጫዎች ዴሞክራሲያዊነት የተረጋገጠ እንዲሆን ኢህአዴግ ግንባር ቀደም ሚና መጫወት ይጠበቅበታል።

የሚካሄዱ ምርጫዎች ዴሞክራሲያዊ እንዲሆኑ ማድረግ ስንል የመጨረሻ ውጤቱ ብቻ ሳይሆን ገና ከመጀመሪያው ጀምሮ ያለው ሂደትም ዴሞክራሲያዊ እንዲሆን ማድረግ ማለታችን ነው። ከመጀመሪያው በተበላሸና ፀረ-ዴሞክራሲያዊ ሂደት ውስጥ ያለፈ ምርጫ ምንም ቢሆን የመጨረሻ ውጤቱ ዴሞክራሲያዊ ሊሆን አይችልም። ስለዚህም ኢህአዴግ የምርጫውን ዴሞክራሲያዊነት ለማረጋገጥ መጫወት ያለበት ግንባር ቀደም ሚና ከዝግጅቱ አንስቶ እስከ የምርጫው የመጨረሻው ተግባር ድረስ ያለው መላ ሂደት ፍፁም ዴሞክራሲያዊ ሆኖ እንዲዘልቅ ማድረግ ላይ ያተኮረ ሊሆን ይገባል።

ዴሞክራሲያዊ ምርጫና የምርጫ ሂደት የህዝብ ሉዓላዊነት ማረጋገጫ ነው። በአንፃሩ በፀረ-ዴሞክራሲያዊ አኳኋን የሚካሄድና የሚጠናቀቅ ምርጫ የህዝብን ሉዓላዊነት የሚጋፋ መሆኑ አያጠያይቅም። ይህም ብቻ ሳይሆን በአገራችን የተረጋጋ ሰላማዊ ሂደት እንዳይኖር እንቅፋት መሆኑም አይቀርም። የምናካሂደው ምርጫ ከሁሉ በፊት የአትዮጵያን ህዝቦች አመኔታ ያተረፈ፣ በመቀጠልም ዓለም አቀፍ ተቀባይነት ያለው እንዲሆን ኢህአዴግና አባል ድርጅቶቹ እንዲሁም የኢህአዴግ አባላትና ደጋፊዎች ሁሉ ህግ አክብረው መንቀሳቀስ ይጠበቅባቸዋል፤ ይገባቸዋልም። አባላትና ደጋፊዎች የአገሪቱን ህጎች አክብረው መንቀሳቀሳቸው እንደተጠበቀ ሆኖ ይህን የምርጫ ሥነ-ምግባር መመሪያ ደግሞ በላቀ ትኩረት ሊያከብሩትና ተግባራዊ ሊያደርጉት ይገባል።

በኢህአዴግ የተዘጋጀው ይህ የምርጫ ሥነ-ምግባር መመሪያ (Code of Conduct) በሦስት ክፍሎች የተዋቀረ ነው፡፡ የመጀመሪያው አጠቃላይ መርሆዎችን ያስቀምጣል፣ መርሆዎቹ የኢህአዴግ ዝርዝር የሥነ-ምግባር መመሪያዎች የተመሰረቱባቸው ገዢ መርሆዎች ናቸው፡፡ በመቀጠልም ዝርዝር መመሪያዎቹ ቀርበዋል፡፡ በመጨረሻው ክፍል የሥነ-ምግባር መመሪያዎቹን ጥሰው የሚገኙ አባላትና ደጋፊዎች ተጠያቂነት ምን እንደሚሆንና እንዴት እንደሚፈፀም ተዘርዝሯል፡፡

መመሪያው በሚፈለገው መንገድ ስራ ላይ እንዲውል በማብቃት በኩል ተቀዳሚው ጉዳይ ሁሉም አባላትና ደጋፊዎቻችን መመሪያውን ሊያውቁት፣ በትክክል ሊገነዘቡትና ተግባራዊ ለማድረግ በአግባቡ ሊዘጋጁ የሚችሉበት ሁኔታ መፈጠሩ ነው፡፡ ከዚህ አኳያ ያሉንን የአባላትና የደጋፊዎች አደረጃጀቶችን በመጠቀም እንዲሁም አግባብ ያላቸውን የአባላትና የደጋፊዎች መድረኮችን በማዘጋጀት በየአካባቢው በቂ ውይይት የሚደረግበትን ሁኔታ መፍጠር ያስፈልጋል፡፡ መመሪያውን ማዳረስ በሚቻለው መጠን በስፋት ወደ አባላትና ደጋፊዎቻችን በመዘርጋትም ከውይይቱ በተጨማሪ በግል ንባብ በመመሪያው ላይ ሊኖራቸው የሚገባውን ግልፅነት የሚያዳብሩበት፣ በምርጫው የለት ተለት እንቅስቃሴም በማገናዘቢያነት የሚጠቀሙበትን ሁኔታ መፍጠር ይኖርብናል፡፡

በመጨረሻም ምንም እንኳ መመሪያው አባላትና ደጋፊዎቻችን በምርጫው ሂደት የሚጠበቅባቸውን ተልእኮ በትክክል እንዲገነዘቡና ከተሳሳተ የምርጫ አፈፃፀም እንዲቆጠቡ ለማድረግ የተዘጋጀ ድርጅታዊ ሰነድ ቢሆንም ከህዝብም ሆነ ከተወዳዳሪዎቻችን የምንደብቀው ምስጢራዊ ሰነድ እንዳልሆነ ሊታወቅ ይገባል፡፡ በመሆኑም መመሪያውን ማየት የሚፈልግ ሁሉ እንዲያገኘው በተመቸው መንገድ ሁሉ ክፍት ማድረግ ይገባል፡፡

## ክፍል አንድ

## የኢህአዴግ የምርጫ ሥነ-ምግባር የሚገዛባቸው ዋና ዋና መርሆዎች

የኢህአዴግ አባላትና ደጋፊዎች እንዲመሩበት የሚፈለገው የምርጫ ስነምግባር መመሪያ ከድርጅቱ መሰረታዊ አላማዎችና አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ባህሪ የሚመነጭ ነው:: በመሆኑም ስንፈልግ የምንይዛቸው ሳንፈልግ ስንቀር ደግሞ የምንተዋቸው ሳይሆን መላ የምርጫውን ሂደት የሚሸፍኑና ሁሉንም እንቅስቃሴያችንን የሚገዙ መሰረታዊ መርሆዎች አሉ:: እንደሚከተለው ይቀርባሉ::

### 1. ምርጫ የህዝብ ሉዓላዊነት ማረጋገጫ ነው፣

በኢህአዴግ እምነት የአገራችን ሉዓላዊነት በወንዝ በተራራ ….. የሚገለፅ ሳይሆን የህዝብ ሉዓላዊነት ማለት ነው:: የአገራችን ህዝቦች በትግላቸው እውን ያደረጉት ሉዓላዊነታቸው በህገ-መንግስታችን በሰፈሩ ግልፅ ድንጋጌዎች የህግ እውቅና አግኝቷል:: ህገ-መንግስታችን የህዝብን ሉዓላዊነት አስመልክቶ በደነገገበት አንቀፅ 8 ላይ የሚከተለውን ይላል፤

1. የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች፣ ህዝቦች የኢትዮጵያ ሉዓላዊ ስልጣን ባለቤቶች ናቸው::
2. ይህ ህገ-መንግስት የሉዓላዊነታቸው መገለጫ ነው::
3. ሉዓላዊነታቸውም የሚገለፀው በዚህ ህገ-መንግስት መሠረት በሚመርጧቸው ተወካዮቻቸው በቀጥታ በሚያደርጉት ዴሞክራሲያዊ ተሳትፎ አማካኝነት ይሆናል::

በዚህ መሠረት በአገራችን የሚካሄዱ ምርጫዎች ሁሉ የህዝቡ ሉዓላዊነት መገለጫዎች ናቸው:: የስልጣኑ ደረጃ የተለያየ ቢሆንም ማንኛውም በህዝብ የሚካሄድ ምርጫ ህዝቡ ፍላጎቱንና ጥቅሙን በማስከበር በኩል በትክክል ይወክለኛል የሚለውን የሚመርጥበት፣ አይወክለኝም የሚለውን ደግሞ ድምፅ የመስጠት ስልጣኑን በመጠቀም ወደ ፖለቲካዊ ስልጣን እንዳይገባ የሚወስንበት ወሳኝ መሳሪያ ነው::

ህዝቡ ይህንን ወሳኝ መሳሪያ ባግባቡ እንዲጠቀምበት መደገፍ፣ መምራት፣ አስፈላጊ በሆነው መስክ ሁሉ ሂደቱ በድል እንዲጠናቀቅ መስራት የህዝቡን ሉዓላዊነት የሚያጠናክር ይሆናል:: የምርጫው ድል የሚወሰነው ደግሞ ህዝቡ በነፃና ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ መሳተፉ ሲረጋገጥ ነው:: በአንፃሩ ማንኛውም ነፃና ዴሞክራሲያዊ ምርጫን የሚያደናቅፍ ወይም የሚጎዳ ተግባር ሁሉ የህዝብን ሉዓላዊነት ይጋፋል:: ህዝቡ በነፃ እንዳይመርጥ፣ የምርጫው ሂደት ዴሞክራሲያዊ በሆነ አኳኋን እንዳይጠናቀቅ በአንድ ወይም በሌላ መንገድ እንቅፋት መፍጠር ዞሮ ዞሮ የህዝቡን ሉዓላዊ የስልጣን ባለቤትነት የማይቀበል አስተሳሰብና ተግባር ከመሆን ውጭ አይሄድም::

መላ የኢህአዴግ አባላትና ደጋፊዎች ምርጫው ዴሞክራሲያዊ ሆኖ እንዲጠናቀቅ ግንባር ቀደም ሚና ወጫወት አለባቸው የምንለው በዚህ መንገድ መስራታችን ጥሩ ስለሆነ ብቻ አይደለም፤ ነፃ፣ ፍትሃዊ፣ ዴሞክራሲያዊና ህጋዊ ምርጫ የህዝቡን ሉዓላዊነት የሚያስከብር፤ የምንገነባው ዴሞክራሲያዊ ስርአት የማእዘን ድንጋይ በመሆኑ እንጂ።

## 2. ሁሉም አማራጮች ለህዝቡ በነፃና በእኩልነት ሊቀርቡ ይገባል

የህዝቡ ሉዓላዊነት በትክክል ሥራ ላይ ሊውል የሚችለው በአገሪቱ የሚገኙ ተወዳዳሪ ሃይሎች በሙሉ አለን የሚሉትን አማራጭ ሃሳብ በነፃና በእኩልነት ለህዝቡ አቅርበው ህዝቡ ከቀረቡለት አማራጮች መካከል ይበልጥ ይጠቅመኛል ያለውን ሲመርጥ ነው። ህዝቡ አማራጭ ሳይቀርብለት ፍላጎቱን በትክክል ሊያንፀባርቅ መቸገሩ አይቀርም። ማንኛውም አስተሳሰብ ወይም አማራጭ በነፃ እንዲቀርብ ካልተደረገ በቀር ትክክለኛነቱ ወይም የተሳሳተ መሆኑ ሊታወቅ አይችልም። የተሳሳተ የሚባልን ሃሳብ ማጋለጥ፣ በትክክለኛ ሃሳብ ዙሪያ ድጋፍ ማሰባሰብ የሚቻለው ሁሉም ሃሳቦች በነፃ ለህዝቡ እንዲቀርቡ በማድረግ ብቻ ነው።

በመሆኑም ሁሉም አማራጮች ገደብ ሳይደረግባቸው ለህዝብ የሚቀርቡበትን ዕድል በቀጣይነት ማስፋት ይገባል። አማራጮች በነፃ የሚቀርቡበትን ዕድል የሚያጠቡና በተለያየ መንገድ እንቅፋት የሚሆኑ አሠራሮች እየተወገዱ አማራጮች የማቅረብ ዕድልን የሚያሰፉ አሰራሮች በሰፊው ጥቅም ላይ እንዲውሉ ሊደረግ ይገባዋል። የተለያዩ ሃይሎች አሉን የሚሉዋቸውን አማራጮች እንዳያቀርቡ አለማደናቀፍ ብቻ ሳይሆን ነፃ ሆነው እንዲያቀርቡ ማደፋፈርና ማበረታታት፣ ሁኔታዎችንም ማመቻቸት ጭምር አስፈላጊ እንደሆነ ሊታመንበት ይገባል።

ይህ መርህ ኢህአዴግ በምርጫ ውድድር ብቻ ሳይሆን በቋሚነት የሚመራበት፣ በአገሪቱ የመልካም አስተዳደርን ከማስፈን አኳያም አበክሮ ሊከተለው የሚገባ መርህ መሆን አለበት። በምርጫ ወቅት ደግሞ የመርሁ መከበር ከመቸውም ጊዜ በላይ ተፈላጊ ነው። በመሆኑም መላ የኢህአዴግ አባላትና ደጋፊዎች ህዝቡ አማራጭ ሃሳቦችን ሁሉ አግኝቶ በመረጃ ላይ የተመሰረተ ውሳኔ እንዲወስን የሚጠበቅባቸውን ሁሉ ማድረግ ይገባቸዋል። በምንም መንገድ ቢሆን አማራጭ ሃሳቦች እንዳይቀርቡ አደናቃፊ ሆነው መገኘት የለባቸውም።

## 3. ሁሉም ፓርቲዎች ህዝቡን በነፃነት የማግኘት መብት አላቸው

አገራችን ዴሞክራሲን በመገንባት ላይ የምትገኝ፣ በህገመንግስት የምትመራ አገር ነች፡፡ የአገራችን ህዝቦች ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ተከብረዋል፡፡ ከአገራችን ህዝቦች ዴሞክራሲያ መብቶች ውስጥ አንዱ ደግሞ በተለያየ አግባብ ተደራጅቶ መንቀሳቀስ፤ የፖለቲካዊ ፓርቲ አባል የመሆን /የህገመንግስቱን አንቀፅ 31 እና አንቀፅ 38/2 ይመልከቱ/ መብት የተከበረ መሆኑ ነው፡፡ በፓርቲም ሆነ በሌላ መልክ የተደራጁ ክፍሎች ደግሞ በከተማም በገጠርም በነፃ ተንቀሳቅሰው ህዝቡን ማግኘት፣ ጽ/ቤት የመክፈት፣ የህዝብ ስብሰባዎችን የመጥራት፣ ስለዓላማቸው ማስተማርና ድጋፍ የማሰባሰብ መብት አላቸው፡፡ ፓርቲዎች ህጉን አክብረው በሚያደርጉት ነፃ እንቅስቃሴ ላይ አንዳችም ገደብ አይጣልባቸውም፤ ሊጣልባቸውም አይገባም፡፡

ፓርቲዎች በነፃ ለመንቀሳቀስ ያላቸውን መብት የምናከብረው ግን ህጋዊ መብታቸው ስለሆነ ብቻ አይደለም፡፡ በአገራችን ልንገነባው ለምንፈልገው መድብለ ፓርቲ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት አማራጭ የሌለው ሰለሆነም ነው፡፡ ሁሉም ፓርቲዎች የሚወክሉትን የህብረተሰብ ክፍል ፍላጎትና ጥቅም በውል ለይተው፣ የተተነተነ ፕሮግራም ይዘው በነፃ መወዳደር የሚችሉበት ሁኔታ በተረጋገጠ መጠን የመቻቻል ባህል እየዳደረ፣ በአብዛኛው ህዝብ የተደገፈ አማራጭ ገዥ ሆኖ ስራ ላይ የሚውልበትና አነስተኛው ደግሞ ሳይደፈቅ ህጋዊና ሰላማዊ በሆነ መንገድ የሚንቀሳቀስበት ዴሞክራሲያዊ ስርአት እንዲዳብር የማይተካ ሚና ይጫወታሉ፡፡

ፓርቲዎች በዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታው በብቃት ሊሳተፉና አሉን የሚሉዋቸውን አማራጮች ለህዝቡ ሊያቀርቡ የመቻላቸው ጉዳይ ደግሞ በነፃነት መንፈስ ለመንቀሳቀስ ከመቻላቸው ጋር በቀጥታ የተያያዘ ነው፡፡ በመሆኑም ማንኛውም የኢህአዴግ አባልና ደጋፊ ፓርቲዎች በነፃ ተንቀሳቅሰው ህዝቡን እንዲያገኙ በየሚመለከተው ደረጃ ሁኔታዎችን የማመቻቸት ሃላፊነት አለበት፡፡ እያንዳንዱ አባልና ደጋፊ ፓርቲዎች ከህዝቡ ጋር እንዳይገናኙ እንቅፋት ከመፍጠር መቆጠብ፣ እንቅፋት የሚፈጥሩ አባላትንና ደጋፊዎችንም መታገል ይጠበቅበታል፡፡

## 4. ህግን አክብሮ መንቀሳቀስ

ኢህአዴግ የዴሞክራሲያዊ ስርአት አንዱ መሰረታዊ ጉዳይ የህግ የበላይነት መከበር እንደሆነ ያምናል፡፡ በአገራችን የህግ የበላይነት እንዲከበርም በፅናት ይታገላል፡፡ የኢህአዴግ አባላት ህገ-መንግስቱንና ሌሎች የአገሪቱን ህጎች በሙሉ የማክበርና የማስከበር የዜግነት ብቻ ሳይሆን የኢህአዴግ አባልነት ግዴታም አለባቸው፡፡ ይህ ደግሞ በምርጫ ወቅት ብቻ ሳይሆን በማንኛውም ጊዜ ሊያሟሉት የሚገባ ተልእኮ ይሆናል፡፡

ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ በምርጫ ወቅት የህግ የበላይነትን ማክበር ከመቼውም ጊዜ የላቀ ፖለቲካዊ ተፈላጊነት አለው፡፡ ምርጫው ነፃና ፍትሃዊ ሊሆን የሚችለው ለሁሉም ተወዳዳሪዎች እኩል እንዲያገለግሉ ሆነው የተቀረፁ የምርጫ ህግና ደንቦች ሲከበሩና በሥራ ላይ ሲውሉ ነው፡፡

ህገመንግስቱ፣ ሌሎች የአገሪቱ ህጎች የምርጫው ህግና ደንብ እንዲሁም የምርጫ ቦርዱ የሚያወጣቸው መመሪያዎች ከተጣሱ ምርጫው ዴሞክራሲያዊ ሆኖ ሊካሄድ አይችልም።

በመሆኑም መላ የኢህአዴግ አባላትና ደጋፊዎች የአገራችንን ህገ-መንግስት፣ ለሎች ህጎችና በተለይም ደግሞ የምርጫ ህጉንና ደንቦችን እንዲሁም የምርጫ ቦርድ መመሪያዎችን በጥብቅ አክብረው መንቀሳቀስ ይገባቸዋል። የህግ የበላይነትን የሚጥሱ ማናቸውንም አዝማሚያዎችና ተግባራትን አምርረው መታገልና ከተፈፀመው ስህተት ጋር የሚመጣጠን ተጠያቂነት እንዲኖር ሊያደርጉ ይገባል።

## 5. ለሁሉም እኩል የሚያገለግል አመቺ የውድድር ሁኔታ መፍጠር፣

ምርጫው ነፃና ፍትሃዊ በሆነ መንገድ መከናወኑ የሚረጋገጠው ሁሉም ተወዳዳሪዎች እኩል የሚስተናገዱበትና የሚገለገሉበት አመቺ የውድድር ሁኔታ ሲፈጠር ነው። በዚህ ረገድ በተለይ በመንግስት በጀት የሚተዳደሩ ተቋማት በሙሉ ለሁሉም ፓርቲዎች እኩል የሚያገለግሉበት ሁኔታ ሊኖር ይገባል። ገዥው ፓርቲም ሆነ የአገሪቱን ህጎች አክብረው በምርጫው የሚወዳደሩ ተቃዋሚ ፓርቲዎች የምረጡኝ ቅስቀሳቸውን ሲያካሂዱ የመንግስትን መገናኛ ብዙሃን፣ የመንግስትን አዳራሾች .... ወዘተ እኩል የመጠቀም መብት መከበር አለበት።

የመንግስት ንብረት /ተሽከርካሪ፣ የጽህፈት መሳሪያ፣ በጀት....ወዘተ./ ለመንግስት ሥራ ብቻ መዋል እንዳለበት፤ ስልጣን ላይ የወጣ ፓርቲ በምርጫ ወቅት የመንግስትን ንብረት በመጠቀም የምረጡኝ ዘመቻ ማካሄድ እንደማይችል በጥብቅ መከበር ይኖርበታል። ገዥው ፓርቲም እንደሌሎቹ ተወዳዳሪዎች ሁሉ የምረጡኝ ዘመቻውን በራሱ አቅም መሸፈን፣ መንግስት ለተወዳዳሪዎች የሚሰጠው ድጋፍ ካለም እንደአገሩ ማግኘት እንጂ ስልጣኑን በምርጫው የተለየ ጥቅም ለማግኘት መጠቀም የለበትም።

ስለዚህ ኢህአዴግ በስልጣን ላይ ያለ ፓርቲ በመሆኑ በመንግስት አቅም አላግባብ እንዳይገለል በተለይም ደግሞ የመንግስትን ንብረት እየተጠቀመ የምረጡኝ ዘመቻ እንዳያካሂድ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ይገባል። መላ የኢህአዴግ አባላትና ደጋፊዎችም ለሁሉም ተወዳዳሪዎች እኩል የሚያገለግል አመቺ የውድድር ሁኔታ መፍጠር እንዳለባቸው ተገንዝበው ይህንን የሚፃረሩ አዝማሚያዎችና ተግባራትን አምርረው መታገል ይጠበቅባቸዋል።

## 6. ከተወዳዳሪ ፓርቲዎች ጋር ተባብሮ መስራት፣

በአገራችን የሚካሄድ ምርጫ የዴሞክራሲ ባህልን በመገንባት ረገድ ቀላል የማይባል ሚና ይኖረዋል። በምርጫው ለመወዳደር ዝግጁ የሆኑ ፓርቲዎች በጋራ እየተወያዩ ለመንቀሳቀስና በምርጫው ሂደት በአሠራርና በአፈፃፀም ዙሪያ የሚታዩ ችግሮችንም በጋራ እየፈቱ ለመጓዝ ከምርጫ የተሻለ ዕድል የሚሰጥ ነገር የለም። በአሠራርና በአፈፃፀም ላይ የሚታዩ ችግሮችን እየፈቱ በጎ ልምዶችን ደግሞ እያዳበሩ ለመጓዝ ገዥው ፓርቲ ከሁሉም ተወዳዳሪ ፓርቲዎች

ጋር አብሮ የሚሰራበትን ሁኔታ ማረጋገጥ ይገባል። ይህን በማድረግም ከተራ አሉባልታና መወነጃጀል የፀዳ፣ በዴሞክራሲና በሰለጠነ የችግር አፈታት መርህ የሚመራ ምርጫ ማካሄድ እንችላለን፤ ይገባልም። በዚህም አገራችን ዴሞክራሲያዊ ምርጫ የማካሄድ ብቃት እንዳላት በተግባር ማረጋገጥ የሚቻልበትን ሁኔ እንፈጥራለን።

ከዚህ አኳያ ኢህአዴግ ህገ-መንግስቱንና ሌሎች የአገሪቱን ህጎች እንዲሁም የምርጫ ቦርድን መመሪያዎች አክብረው በሰላማዊና ህጋዊ መንገድ ለመንቀሳቀስና በምርጫው ለመሳተፍ ከወሰኑ ፓርቲዎች ጋር በየደረጃው የጋራ ኮሚቴዎች በማቋቋም፣ በጎ ጅምሮችን በጋራ ስምምነት በማስፋፋት፣ ጎጂ አዝማሚያዎችን ደግሞ በጋራ በመታገል ምርጫው በርግጥም ነፃ፣ ህጋዊና ፍትሃዊ ሆኖ እንዲካሄድ የበኩሉን ገንቢ ሚና ይጫወታል። ይህ ግን ህጋዊውንና ህገ-ወጡን መንገድ እያጣቀሱ ለመንቀሳቀስ የሚጥሩትን ሃይሎች የሚመለከት አይደለም። በምርጫው ለመንቀሳቀስም ሆነ አላማቸውን በነፃ ለማራመድ ያላቸውን ህገ-መንግስታዊ መብት የማንጋፋ ቢሆንም በምርጫው ሂደት ከነዚህ ሃይሎች ጋር የጋራ ኮሚቴ ማቆምም ሆነ አብሮ መስራት የምንችልበት ሁኔታ አይኖርም። ሁለቱንም እያጣቀሱ ለመሄድና ምርጫው በሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ አኳኋን እንዳይጠናቀቅ ለማደናቀፍ የሚያደርጉትን ጥረት ማጋለጥ፤ እንደአስፈላጊነቱም በህግ የሚጠየቁበትን ሁኔታ መፍጠር ይገባል።

በመሆኑም መላ የኢህአዴግ አባላትና ደጋፊዎች በዚህ መርህ ላይ ግልፅ ሆነው ለተግባራዊነቱ በብቃት መንቀሳቀስ ይጠበቅባቸዋል።

## 7. የተቋማትን ነፃነት ማክበር፣

ምርጫ በሚካሄድበት ወቅት በርካታ ነፃና ገለልተኛ ተቋማት የሚሳተፉበት ሁኔታ ይኖራል። የምርጫ ቦርድ፣ የምርጫ ታዛቢዎች፣ ምርጫን በሚመለከት መራጩን ህዝብ እናስተምራለን ብለው የሚንቀሳቀሱ የተለያዩ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት፣ ፍርድ ቤቶችና ሌሎችም ተቋማት ሁሉ ከምርጫው ጋር የተያያዘ ሥራ ይሰራሉ። እነዚህ ተቋማት ሥራቸውን በገለልተኝነትና በነፃነት የሚሰሩበትን ሁኔታ ማረጋገጥ ለምርጫው ነፃና ፍትሃዊ መሆን አንዱ ዋስትና እንደሆነ ይታመናል። ዋነኛው ጉዳይ ህዝቡ በሁሉም የምርጫ ተግባራት በስፋት እንዲሳተፍና የምርጫውን ነፃና ፍትሃዊነት እንዲያረጋግጥ ማድረግ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በምርጫው የሚሳተፉ ተቋማት ተገቢውን ሚና እንዲጫወቱ ማድረግም ትኩረት ሊሰጠው ይገባል።

የተቋማቱን ብቁ ተሳትፎ የማረጋገጡ ተግባር በዋነኛነት በራሳቸው የሚፈፀም ሲሆን በኛ በኩል ከፍተኛ ጥንቃቄ ሊደረግበት የሚገባው ተቋማዊ ነፃነታቸውን የማክበርና ያለመጋፋት ጉዳይ ነው። በመሆኑም መላ የኢህአዴግ አባላትና ደጋፊዎች በምርጫው ውስጥ ቀጥተኛም ሆነ ተዘዋዋሪ ሚና ያላቸውን ተቋማት ነፃነት በጥብቅ ማክበር ይገባቸዋል። የነዚህን ተቋማት ነፃነት

የሚጋፋ አዝማሚያና ተግባር ከየትኛውም ወገን ይምጣ አምርረው መታገልና ማስወገድ ይገባቸዋል፡፡

## 8. ችግሮችን በውይይት ለመፍታት ቅድሚያ መስጠት፣

በአገራችን የሚካሄድ ምርጫ ችግሮች የሌሉበትና ፍፁም ዴሞክራሲያዊ ሆኖ እንዲፈፀም የማድረግ ጉዳይ መቸም የማይለወጥ የድርጅታችን የምርጫ ግብ ይሆናል፡፡ በምርጫው ሂደት ከኛ በኩል አንዳችም ችግር እንዳይፈጠር አስፈላጊውን ጥንቃቄ ሁሉ እናደርጋለን፡፡ ይሁንናም ከእኛም ሆነ ከሌላውም ወገን ችግሮች ፈፅሞ ሊከሰቱ አይችሉም የሚል ማረጋገጫ መስጠት አይቻልም፡፡ ምናልባት ማረጋገጫ መስጠት የሚቻል ነገር ቢኖር የሚከሰቱት ችግሮች አነስተኛና ጥቃቅን እንዲሆኑ፣ አንዴ የታዩ ችግሮች ሌላ ጊዜ እንዳይደገሙ ማድረግ በሚለው ክልል ብቻ ይሆናል፡፡

ጥቃቅንና ብዙም ትርጉም የማይሰጣቸው ችግሮች ሊከሰቱ ይችላሉ ማለት ግን እንደነዚህ አይነት ችግሮች እንዲኖሩ እንፈቅዳለን ማለት አይደለም፡፡ እንዳይከሰቱ ከምናደርገው ትግል ጎን ለጎን ከተከሰቱም በኋላ በዴሞክራሲያዊና ህጋዊ መንገድ ለመፍታት እንሠራለን ማለት ነው፡፡ በምርጫው ሂደት በተቃዋሚዎችም ሆነ በእኛ በኩል የሚፈፀሙ ስህተቶችን ለፖለቲካ መጠቀሚያ ከማዋል ይልቅ ፈጥኖ በማስተካከል ለቀጣዩ ሂደት የልምድ መቅሰሚያ ሆነው ቢያገለግሉ እንመርጣለን፡፡ ከዚህ አኳያ በምርጫው በሚወዳደሩ ሃይሎች ዘንድ የሚታዩ ችግሮችን በገንቢ መንፈስ ማረምና ማስተካከልን፤ ችግሮች ሲከሰቱ ከሚመለከታቸው ሃይሎች ጋር በመወያየት መፍታትን እንደመሠረታዊ መርህ እንወስዳለን፡፡

በዚህ ረገድ የኢህአዴግ አባላትና ደጋፊዎች ከሁሉ አስቀድሞ በምርጫው ሂደት ችግር እንዳይፈጥሩ መንቀሳቀስ፣ በሌሎች ሃይሎች ስህተቶች ላይ ጣታቸውን ከመቀሰራቸው በፊት በራሳቸው በኩል የሚጠበቅባቸውን በትክክል መወጣታቸውን መፈተሽና ጉድለቶች መኖራቸውን ባወቁ መጠንም ፈጥነው ማስተካከል ይኖርባቸዋል፡፡ አግባብ ያልሆነን ጉዳይ ሌሎች ካደረጉት እኛም እናድርገው ከሚል አጉል የመበለጥ ስሜት መቆጠብ፤ የስህተት ተባባሪ ሆነው የማይገኙበትን ሁኔታ መፍጠር ይጠበቅባቸዋል፡፡

# ክፍል ሁለት

## ዝርዝር የሥነ-ምግባር መመሪያዎች

## 1. ህዝብን ስለምርጫው አስፈላጊነትና አፈፃፀም ለማስገንዘብ የምንከተለው ስነምግባር፤

- ህዝብ በምርጫው በንቃት መሳተፉ፣ በነቂስ ለመራጭነት መመዝገቡና መምረጡ ለምርጫው ዴሞክራሲያዊነት ወሳኝ መሆኑን ተገንዘበ፣

- ህዝቡ ለምርጫው በራሱ ፍላጎት ብቻ መመዝገብና መምረጥ እንዳለበት በፅናት ተገንዘብ፣
- ህዝቡ ለመራጭነት እንዲመዘገብና በምርጫው እለትም ተገኝቶ እንዲመርጥ አስተምር እንጂ አታስገድድ፣
- ህዝቡ ለመራጭነት እንዲመዘገብና በድምፅ መስጫ እለትም ተገኝቶ እንዲመርጥ አሳማኝና ዴሞክራሲያዊ አግባቦችን ብቻ ተጠቅመህ አስተምር፣
- ለመራጭነት እንዲመዘገብ ህዝብን ስታስተምር ተቃዋሚ ሊሆን ይችላል የምትለውን እየለየህ ደጋፊ የሚባለውን ብቻ አታስተምር፤ ሁሉም ዜጋ ህገ-መንግስታዊ መብቱን እንዲቀጠም አስተምር፣
- ለመራጭነት ሊመዘገብ የመጣን ወገን ተቃዋሚ ወይም ደጋፊ ነው በሚል በተለያዩ ሰበቦች የመመዝገብና የመምረጥ መብቱን አትጋፋ፣
- ለምርጫው ለመመዝገብ የሚሄድን ወይም የተመዘገበን ሰው የየትኛው ፖለቲካ ፓርቲ ደጋፊ ስለመሆኑ ከመጠየቅ ተቆጠብ፣
- ዕድሜው ለመራጭነት ያልደረሰን ግለሰብ ይደግፈናል ከሚል ሃሳብ በመነሳት እንዲመዘገብ መቀስቀስ የለብህም፣
- ህዝቡ ለመራጭነት እንዲመዘገብ የተለያዩ አስተዳደራዊና ማህበራዊ ተፅዕኖዎችን ለማሳደር አትሞክር፣
- የተለያዩ መንግስታዊ አገልግሎቶችን ለመራጭነት ምዝገባ መደለያ ማድረግ ወይም መንግስታዊ አገልግሎት ለማግኘት ምዝገባንና ምርጫን እንደ ቅድመ ሁኔታ ከማድረግ ተቆጠብ፣
- እርዳታ፣ የገጠር ፋይናንስ ብድርና የመሳሰሉ አገልግሎቶችን በምንም ሁኔታ ከምርጫው መመዝገብና መሳተፍ ጋር ለማያያዝ አትሞክር፣
- የመራጮችን ምዝገባ በህጉ መሠረት በተፈቀደው ቦታ ብቻ መካሄዱን ተከታተል፤ ከዚህ ውጭ በሆነ መንገድ ምዝገባ እንዲካሄድ አንዳችም አይነት ጥረት አታድርግ፣

## 2. በምረጡኝ ቅስቀሳ ወቅት ልንከተለው የሚገባ ሥነ-ምግባር፤

- ቅስቀሳህ የነፃና ፍትሃዊ ምርጫ መርህን የተከተለ እንዲሆን አድርግ፣
- መራጩ ህዝብ የሁሉንም ተወዳዳሪ ፓርቲዎችና ግለሰቦች ሃሳቦችን በነፃነትና በእኩልነት የማግኘት መብቱን በፅናት አክብር፣
- ሁሉም ተወዳዳሪ ፓርቲዎችና ግለሰቦች በሁሉም የሃገሪቱ አካባቢዎች በነፃ ተንቀሳቅሰው ዓላማቸውን የማስረዳትና የምረጡኝ ቅስቀሳ የማድረግ ነፃነታቸውን በምንም ሁኔታ አትጋፋ፣

- ተወዳዳሪ ፓርቲዎች በምርጫው ሂደት የማንንም ፈቃድ ሳይጠይቁ ደጋፊዎቻቸውን የማሰባሰብ፣ ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግና ሌሎች የቅስቀሳ አግባቦችን የመጠቀም መብታቸውን አትገድብ፣
- ተወዳዳሪ ፓርቲዎች እንዲከራከሩ በሚፈጠሩ መድረኮች ሁሉም ፓርቲ ሃሳቡን በነፃ እንዲያራምድ፤ ሁሉም እኩል የመናገሪያ ጊዜ እንዲያገኙ አድርግ፣
- በመጮህና በመንጫጫት ስብሰባዎችን ከማወክ ተቆጠብ፣
- በክርክር ወቅት ተወዳዳሪዎች የሚያነሱት ሀሳብ ተቃወም እንጂ የሃሳብ አቅራቢዎችን ስብእና የሚጎዱ ሃሳቦችን ከማቅረብ ተቆጠብ፣
- ቤት ለቤት ተዘዋውረህ ስትቀሰቅስ መራጮችን በትህትና ቅርብ፤ ካልፈቀዱ በስተቀር ወደግለሰቦች ቤት አትግባ፣
- በአካባቢው ባለስልጣን በመሆንህ የምትታወቅ ከሆነ አመጣጥህ የመንግስት ስልጣንህን ወክለን በመንግስት ጉዳይ ለማወያየት ሳይሆን በድርጅት አባልነትህ የምረጡኝ ቅስቀሳ ለማካሄድ እንደሆነ ቀድመህ አስረዳ፣
- የተወዳዳሪዎችን ስብሰባ ለማደናቀፍ ከመሞከር ተቆጠብ፣
- ለሁሉም ህዝብ ክፍት ካላደረጉት በስተቀር ተቃዋሚዎች በጠሩት ስብሰባ ላይ አትገኝ፣
- ለሁሉም ህዝብ ክፍት በሆነ የተቃዋሚዎች ስብሰባ ስትገኝም ካልተፈቀደልህ አትናገር። የምትናገረው ጠይቀህ ከተፈቀደልህ ብቻ ይሁን፣
- የመናገር እድል ስታገኝ ሀሳብህን ግልፅና አጭር አድርገህ አቅርብ፤ የተንዛዛ ንግግር በማድረግ የስብሰባ ጊዜያቸውን አታባክን፣
- በምረጡኝ ዘመቻው ሁሉ ለህዝቡ ትክክለኛ መረጃዎችን ብቻ ስጥ፤ ማጭበርበር፣ የማይገባ ተስፋ መስጠትና መደለል አጥብቆ የተከለከለ ነው፣
- በመድረኮች በሚደረጉ ውይይቶች ከማንም ይምጣ ከማን የተቃውሞ ሃሳቦችን በሙሉ በትእግስት አዳምጥና አስጨርስ፤ የተቃውሞ ሀሳብን በርጋታ የማዳመጥ ባህልን ማበረታታት አለብህ፣
- የተቃወሙ ሰዎችን በምርጫው ሂደትም ሆነ ከምርጫው በኋላ በተለያዩ አስተዳደራዊና ፖለቲካዊ ሰበቦች መጉዳት አይገባም፣
- በምርጫ ህጉ መሰረት ለቅስቀሳ ባልተፈቀዱ ቦታዎች ማለትም በወታደራዊ ካምፖች፣ በሃይማኖት ተቋማት፣ ትምህርት በሚካሄድባቸው ት/ቤቶች፣ የመንግስት መደበኛ ስራዎች በሚካሄዱባቸውና መሰል ቦታዎች ቅስቀሳ አታድርግ፣
- በጥቅሉ ምርጫው የህዝብ ሉአላዊነት መገለጫ መድረክ መሆኑን ተገንዝበህ ህዝቡ የሚ ቀርቡለትን አማራጮች ሁሉ በነፃነት አግኝቶ የመወሰን መብቱን በምንም ሁኔታ አትጋፋ፣

## 3. ተወዳዳሪ ፓርቲዎችና ግለሰቦችን በሚመለከት መከተል ያለብን ስነ-ምግባር፣

- የተወዳዳሪ ፓርቲዎችና ግለሰቦች ተሳትፎ ለምርጫው ዴሞክራሲያዊነት ያለውን ወሳኝ ሚና በአግባቡ ተገንዘብ፤ ተወዳዳሪዎችን ሁሉ በእኩልነትና በፍትሃዊነት አስተናግድ፣ አበረታታ፣
- ተወዳዳሪ ፓርቲዎችን በአካባቢው በነፃ እንዳይንቀሳቀሱ፣ ጽ/ቤት እንዳይከፍቱ እንቅፋት አትፍጠር፣
- በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የተወዳዳሪዎችን የምረጡኝ ቅስቀሳ ለማደናቀፍ መሞከር አጥብቆ የተከለከለ ነው፣
- የተወዳዳሪዎችን የቅስቀሳ እቅድ ቀድመህ በማወቅ እቅዳቸውን ለማደናቀፍ አትሞክር፣
- ተወዳዳሪ ፓርቲዎችን የወከሉና በግል የቀረቡ እጩዎችን በማናቸውም አስተዳደራዊና ፖለቲካዊ ተፅእኖዎች ከማደናቀፍ ተቆጠብ፣
- ተወዳዳሪ እጩዎችን ከምርጫ ሕጉና ከሚመለከታቸው አካላት ውጪ በህግ መጠየቅ፣ ማሰር እንማይቻል ተገንዘብ፣
- የመንግስት ሰራተኞች የሆኑ የተወዳዳሪ ፓርቲዎችና የግል እጩዎችን በአስተዳደራዊና ቢሮክራሲያዊ አግባቦች ተጠቅመህ ተዘዋውሮ የመቀስቀስ መብታቸውን አትገድብ፣
- የተወዳዳሪ ፓርቲዎችና የግል ተወዳዳሪ እጩዎችን፣ ቤተሰቦቻቸውንና ዘመዶቻቸውን በተለያዩ አስተዳደራዊ፣ ፖላቲካዊና ማሕበራዊ ተፅእኖዎች ለማሸማቀቅ አትሞክር፣
- ለተወዳዳሪዎቻችን የተሟላ፣ ነፃና ዴሞክራሲያዊ ተሳትፎ እድል የሚነፍግ ማናቸውንም አደናቃፊ ሁኔታ አትፈጠር፣
- በምርጫው በማሸነፍም ሆነ ተሳትፎ በመሸነፍ ምክንያት ከምርጫው በፊትም ሆነ በኋላ በተወዳዳሪዎች እጩዎች ላይ የተለየ ጫና ለመፍጠር አትሞክር፣
- የግል ተወዳዳሪዎች የድጋፍ ፊርማ ማሰባሰብ ሂደትን አበረታታ በሂደቱም አግዛቸው፣
- የድጋፍ ፊርማን ትክክለኝነት የማጣራት ስራ አይመለከትህም፤ ማንኛቸውንም አይነት የማጣራት ስር ለመስራት አትሞክር፤
- በጥቅሉ በተወዳዳሪ እጩዎች ላይ ማንኛውንም አስተዳደራዊና ፖለቲካዊ እርምጃ መውሰድ ክልክል ነው፣
- የተወዳዳሪ ፓርቲዎችና የግል እጩዎችን የቅስቀሳ ፖስተር በራሪ ወረቀትና ባነሮችን መቅደድም ሆነ ማበላሸት በጥብቅ የተከለከለ ነው፣

## 4. ተወዳዳሪዎች ስህተት ፈፅመው ሲገኙ መከተል ያለብን ስነ-ምግባር፣

- በቅድሚያ ከተወዳዳሪዎች በዋነኛነትም ሰላማዊና ህጋዊ መንገድን መርጠው ከሚሳተፉ ፓርቲዎች ጋር የሚኖረንን ግንኙነት የመደማመጥ፣ የመከባበርና የመቻቻልን መርህ የተከተለ እንዲሆን አድርግ፣
- ተወዳዳሪዎች ፈፅመውታል የሚባል ስህተት በተጨባጭ መረጃዎች ላይ መመስረቱን አረጋግጥ፣
- የሃሰት መረጃ በመያዝ በምንም ሁኔታ ተወዳዳሪዎችና ደጋፊዎቻቸውን አትክሰስ፣
- ሁሌም የተፈፀመውን ስህተት ክብደትና በምርጫው ላይ የሚኖረውን ተፅእኖ በአግባቡ አመዛዝን፣
- በሰላማዊና ህጋዊ መንገድ የሚንቀሳቀሱ ፓርቲዎች አባላትና ደጋፊዎች ስህተት ፈፅመው ሲገኙ ችግሩን ፈጥነህ ለፓርቲዎቹ በማስረዳት ለማረም ሞክር፣
- ለመታረም የማይፈቅዱ ከሆነ የተፈፀሙትን ችግሮች አስመልክቶ በተጨባጭ መረጃ አስደግፈህ ለህዝብ አጋልጥ ለሚመለከታቸው አካላትም አቅርብ፣
- ህጋዊና ህገ-ወጥ መንገድን እያጣቀሱ የሚንቀሳቀሱ ሃይሎች የሚፈጥሩዋቸውን ችግሮች በቅርብ እየተከታተልክ ለህዝብ አጋልጥ፣ አስፈላጊ በሆነበትም ለሚመለከተው ህጋዊ አካል አቅርብ፣
- የሚመለከታቸው አካላት ተገቢውን ህጋዊ እርምጃ እንዲወስዱ በዴሞክራሲያዊ አግባብ ታገል፣

## 5. ከተለያዩ ተቋማት ጋር በሚኖረን ግንኙነት መከተል ያለብን ስነ-ምግባር፣

### 5.1 ከምርጫ ቦርድ፣ ከፅ/ቤቱና ከምርጫ አስፈፃሚዎች ጋር ስለሚኖረን ግንኙነት፣

- ከቦርዱ፣ ከፅ/ቤቱና በየደረጃው ካሉት የምርጫ አስፈፃሚዎች ጋር የሚኖረን ግንኙነት የተቋሙን ነፃና ገለልተኝነት መርህ የተከተለ መሆን አለበት፣
- በምርጫ ቦርድ መመሪያዎች የተከለከሉ ተግባራትን አትፈፅም፤ በተለይ የድርጅት አባል በምርጫ አስፈፃሚነት ተመድቦ መስራት የተከለከለ በመሆኑ በራስህ ፈቃድ በምርጫ አስፈፃሚነት ለመስራት አትጠይቅ፣
- የምርጫ ቦርድ ወይም አስፈፃሚ አካላት የፓርቲ አባልነትህን ባለማወቅ በምርጫ አስፈፃሚነት እንድትሰማራ ቢመድቡህ የፓርቲ አባል መሆንህን አሳውቀህ ምደባውን አትቀበል፤ የምርጫ አስፈፃሚ የሆኑ አባላት ካወቅህም አጋልጣቸው፣
- በእምነት ቦታዎች /ቤተክርስቲያንና መስጊድ/፣ በትምህርት ቤቶች... ወዘተ... የምረጡኝ ቅስቀሳ ስራ ማካሄድ አይቻልም የሚለውን የምርጫ መመሪያ በጥብቅ አክብር፣

- በምርጫ ቦርዱ የምርጫ አስፈፃሚዎች ምደባና ስምሪት ስራ ጣልቃ አትግባ፣
- ምርጫ አስፈፃሚዎች ገለልተኛ እንዲሆኑና ተግባራቸውንም በነፃነት እንዲፈፅሙ የበኩልህን ጥረት አድርግ፣
- የምርጫ አስፈፃሚዎች ለምርጫው ስራ መሳካት አስፈላጊዎች የሆኑ ህጋዊ ትብብሮችን በሚጠይቁበት ጊዜ ሁሉ ተባበር፣
- የመንግስት ሰራተኛ በሆኑ የምርጫ አስፈፃሚዎች ላይ በመንግስት ሀላፊነትህ የተለያዩ ተፅእኖዎች አታድርስባቸው፣
- ቦርዱ ከተወዳዳሪዎች ጋር የምንሰራበት የጋራ መድረክ ለመፍጠር ወይም በየደረጃው የጋራ ኮሚቴ የማቋቋም ጥያቄ ሲያቀርብ በፍላጎት ተሳተፍ፤ ለመድረኩ ዴሞክራሲያዊነት የበኩልህን አበርክት፣
- ለምርጫ አስፈፃሚዎች መደለያ ወይም የተለያዩ ተስፋዎችን በመስጠትና በማግባባት እንዲወግኑን ማድረግ አትችልም፤ ይህንን ማድረግ ወንጀል ነው፣
- አድልዎ የሚፈፅሙ አስፈፃሚዎች ሲያጋጥሙህ አጋልጣቸው፣

## 5.2 የፀጥታና ፍትህ ተቋማትን በተመለከተ መከተል ያለብን ስነ-ምግባር፣

- የፀጥታና ፍትህ ተቋማት በምርጫው ሂደት ነፃና ገለልተኛ ሆነው መንቀሳቀስ አለባቸው፣
- የፖሊስና ሌሎች የፀጥታ ሀይሎች በምርጫው ሂደት በጥበቃ እንዲሰማሩ ጥያቄ መቅረብና መፈፀም ያለበት በምርጫ ቦርዱ ብቻ መሆኑን ተገንዘብ፣
- እነዚህን ተቋማት የሚመሩ አባሎቻችንም ሆኑ ደጋፊዎች ተቋማቱን እንዲሁም ሰራተኞቻቸውን ለገዥው ፓርቲ የምርጫ ስራ ማሰማራት አይችሉም፣
- የፖሊስ ወይም ሌሎች የፀጥታ አስከባሪ ሀይሎች፣ ማዘጋጃ ቤቶች... ወዘተ. በማንኛውም ሰበብ የተቃዋሚዎችን እጩዎች ማሰር ወይም ማንገላታት አይገባቸውም። እንዲህ ሚያደርጉ አካላት ላይ ጠበቅ ያለ ህጋዊ ርምጃ የመውሰድ ግዴታ እንዳለብህ አትዘንጋ፣
- የፍትህና የፀጥታ ተቋማቱን የምርጫውን ዴሞክራሲያዊነት እንዲጎዱ እድል በሚሰጡና ተአማኒነታቸውን በሚጋፉ ማናቸውም ተግባር ላይ እንዲሰማሩ ማድረግ በጥብቅ የተከለከለ ነው፣
- የምርጫውን ሂደት የሚያዛባ ጥፋት በፈፀመ በማንኛውም አካልና ግለሰብ ላይ ህጋዊ ርምጃ እንዳይወሰድ አታደናቅፍ፣
- ፍርድ ቤቶች የቀረበላቸውን ክስ በነፃ፣ በህግና በህሊናቸው ተመርተው እንዳይወስኑ እንቅፋት አትፍጠር፣

## 6. ታዛቢዎችን በተመለከተ መከተል ያለብን ስነ-ምግባር፣

- በምርጫው ሂደት ገለልተኛ የሀገር ውስጥና የውጭ ታዛቢዎች መሳተፍ የሚኖረውን መልካም አስተዋፅኦ በአግባቡ ተገንዘብ፣
- የአገር ውስጥ ታዛቢዎች የሚከተሉት መብቶች እንዳሏቸው ተገንዝበህ መብቶቻቸውን አክብር፣
  - ሀ. በሃገሪቱ በሁሉም አካባቢ በነፃ የመንቀሳቀስ፤
  - ለ. ገለልተኛ ሆነው የምርጫውን ሂደት መታዘብ፤
  - ሐ. ከሁሉም የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ የፓርቲዎችና የግል እጩዎች፣ ሲቪል ማሕበራት..... ጋር በነፃ የመነጋገር መብት፤
  - ረ. ተፅእኖ በማይፈጥሩበት ሁኔታ የምርጫ አስፈፃሚዎችን በነፃ የማነጋገር መብት፤
  - ሰ. ፍ/ቤቶችን፣ የህዝብ ምክርቤቶችን፣ የደህንነትና ፀየጥታ አካላትንና በአጠቃላይም የምርጫ ስራ የሚመለከታቸውን የመንግስት አካላትና ተቋማት በሙሉ በነፃ የማነጋገር መብት፤
  - ሸ. ምርጫውን ለማስፈፀም የወጡ ህጎችና መመሪያዎችን የማግኘት መብት፤
  - ቀ. የመራጩን ህዝብ የመምረጥ ነፃነት በማይጋፋ አኳኋን የድምፅ መስጫ ጣቢያዎችና የቆጠራ ሂደቱን የመመልከት፤
- ከውጭ ታዛቢዎች አኳያ አለም አቀፍ ተቀባይነት ያላቸውን የታዛቢዎችን መብቶች በጥንቃቄ አውቀህ በምንም ሁኔታ መብቶቻቸውን አትገድብ፣
- ታዛቢዎች መብት ብቻ ሳይሆን ግዴታዎችም እንዳሉባቸው ተረድተህ ግዴታዎችን በአግባቡ መወጣታቸውን ተከታተል፣
- ግዴታቸውን ሳይወጡ ሲቀሩ ለሚመለከተው አካል አሳውቅ፣
- ታዛቢዎች ገለልተኛ ሆነው ነፃና ትክክለኛ ምስክርነት እንዲሰጡ አስተምር፣
- ምርጫን የመታዘብ ስራ ድምፅ ከሚሰጥበት ቀን ቀደም ብሎ የሚጀመር በመሆኑ ታዛቢዎች አስቀድመው ወደ ስራ ቢገቡ በነፃ ተንቀሳቅሰው ሂደቱን እንዳይታዘቡ አትከልክል፣
- ታዛቢዎች እውነተኛውንና ትክክለኛውን መረጃ እንዲያገኙ የበኩልህን ጥረት አድርግ፣
- የምርጫውን ሂደት ከታዛቢዎች ለመሸፈን ወይም ለመደበቅ ምንም አይነት ጥረት ከማድረግ ተቆጠብ፣
- ታዛቢዎች ጥርጣሬ እንዲያሳድሩ የሚያደርጉ አቀራረቦችንና ግንኙነቶችን አስወግድ፤ የምታውቀውንና የሆነውን ነገር በግልፅ አስረዳ፤ ገሃድ የሆነን ጉዳይ ለመደበቅ አትሞክር፣

## 7. የመንግስትና የተቋማትን ሃብት አጠቃቀም ላይ መከተል ያለብን ስነ-ምግባር፣

- ገዥ ፓርቲ በመሆናችን በእጃችን የሚገኙትን ማንኛውንም የመንግስት ሃብትና ንብረት በመጠቀም የምርጫ ቅስቀሳ ስራ መስራት እንደማንችልና እንደማይገባ ተገንዘብ፣
- በሃላፊነት የምንመራቸውን መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና ማህበራት እንዲሁም የኢንዶውመንት ተቋማት… ወዘተ. ንብረትም የህዝብ እንጂ የድርጅት ሃብት ስላልሆነ ለምረጡኝ ቅስቀሳ መጠቀም እንደማይቻል ተገንዘብ፣

✓ የመንግስትና የተቋማትን ተሽከርካሪ በመጠቀም ለምረጡኝ ቅስቀሳ መንቀሳቀስ አትችልም፤

✓ የመንግስት መ/ቤቶችንና የተቋማትን ወረቀት፣ ማባዣ፣ ፎቶ ኮፒዎች… ወዘተ… ለምረጡኝ ቅስቀሳ ፅሁፎች ዝግጅት መጠቀም አጥብቆ የተከለከለ ነው፤

- ለምርጫ ስራ ልንጠቀምባቸው የሚችሉ የመንግስትና የሕዝብ ሃብቶችን ከተወዳዳሪዎች ጋር በፍትሃዊነትና በእኩልነት ተጠቀም፤
- ተወዳዳሪዎች ለምርጫ ቅስቀሳ የሚጠይቁትን የመሰብሰቢያ አዳራሽና ሌሎችም ቦታዎችን በተለያዩ ሰበቦች አትከልክል፤
- እኛ ቀደም ብለን የጠየቅንና ህዝቡንም ጥሪ ያደረግን ካልሆነ በቀር ሌሎች ፓርቲዎች እንደሚሰበሰቡበት እያወቅህ የመሰብሰቢያ ቦታውን አትጫረት፤
- መንግስት በሚያወጣው መመሪያ መሰረት ሁሉም ተወዳዳሪዎች በመንግስት ሚዲያ በእኩልነትና በፍትሃዊነት እንዲጠቀሙ አድርግ፤

## 8. በድምፅ መስጫ እለት መከተል ያለብን ስነ-ምግባር፣

- የምርጫ ሕጉ በምርጫው እለት እንዳይፈፀሙ የሚከለክላቸውን ተግባራት በሙሉ አትፈፅም:: በተለይ:-

✓ ህጋዊነት የሌለው የምርጫ ወረቀት አለመያዝ፤

✓ ከመታወቂያ ወረቀትና የምርጫ ካርድ ውጭ አንዳችም ወረቀት ይዘህ ወደ ምርጫ ጣቢያ አለመግባት፤

✓ በምርጫ ኮሮጆ ውስጥ አስቀድሞ አንዳችም አይነት ወረቀት አለማስገባት፤

✓ ድምፅ በሚሰጥበት ወቅት ከራስህ የምርጫ ወረቀት በስተቀር የሌላ ሰው የምርጫ ወረቀት አለመያዝ፤

✓ የሌላ ሰው መልእክተኛ ሆነህ ድምፅ አለመስጠት፤

- ✓ የምርጫ ሳጥን የታሸገበትን ወረቀት አለመንካትና በአጠቃላይ ድምፅ ለመስጠት ካልሆነ በስተቀር የምርጫ ሳጥን/ኮሮጆን አለመጠጋት፤
- ✓ በድምፅ መስጫ ኮሮጆ አጠገብ ለረጅም ጊዜ አለመቆየት ስራህን ቶሎ አጠናቅቀህ መጨረስና ከአካባቢው መራቅ፤
- ድምፅ የመስጠቱን ሂደት የሚያደናቅፍ ማናቸውንም ተግባር አትፈፅም፤
- በምርጫ ህጉ መሰረት ከድምፅ መስጫ ቦታ 500 ሜትር ክልል ውስጥ ገብተህ ቅስቀሳ አታድርግ፤
- የቅስቀሳ ፖስተሮችን፣ ቲሸርቶችን የእጩ ምልክትና መሰል ነገሮችን ይዘህ ከተፈቀደው አካባቢ ውጭ በድምፅ መስጫው አካባቢ አትገኝ፤
- መራጩ ህዝብ የሚፈልገውን ድርጅትና ግለሰብ ለመምረጥ ያለውን መብት በምንም ሁኔታ አትጋፋ፤
- ሁሉም ሰው ወደ ምርጫ ጣቢያው ሲመጣ ማንን መምረጥ እንዳለበት በግሉ ወስኖ እንደሚመጣ ተገንዘብ፤ በዚህም መሰረት በምርጫው እለት በተለይም መራጩ ተራውን ለመጠበቅ በተሰለፈበት ሁኔታ፡-
- ✓ በመራጩ መካከል እየገቡ የመራጩን ውሳኔ የሚያዛቡ ሰዎች አታሰማራ፤
- ✓ መራጩ አስተያየቱን እንዲቀይር ለማድረግ አትሞክር፤
- ራስህ በምትመርጥበት ጊዜ ካልሆነ በስተቀር ወደ ሚስጢር ድምፅ መስጫ ቦታ አትግባ፤
- ርዳታ የሚሹ ወገኖች ማን እንደሚረዳቸው የመምረጥ መብት የራሳቸው ብቻ ነው፤ ስለነሱ በመሆን ረዳቶችን መመደብ አትችልም፤
- ድምፅ የመስጠቱን ስራ ማስጀመርም ሆነ ማስቆም የምርጫ አስፈፃሚዎች እንጂ ያንተ ተግባር ባለመሆኑ ጣልቃ አትግባ፤
- የሕዝቡን ነፃና ፍትሃዊ የምርጫ ውጤት በፀጋ ለመቀበል ራስህን አዘጋጅ፤
- በድምፅ አሰጣጥ ሂደት የህዝቡን በነፃ የመምረጥ መብት የሚገፋ ተግባር በየትኛውም ወገን እንዳይፈፀም በፅናት ታገል፤ ተፈፅሞ ሲገኝም በህጋዊ አግባብ እንዲስተካከል የበኩልህን ትግል አድርግ፤

## 9. የእጩዎቻችን ታዛቢዎች ሊከተሉት የሚገባ ስነ-ምግባር፣

- የድርጅታችን እጩ ተወካይ ሆነህ በታዛቢነት ስትመደብ በተገቢው ሰአት በምርጫው ቦታ ተገኝ፤ ሆኖም ወደ ድምፅ መስጫ ጣቢያው የምትገባው ሁሉም ወይም አብዛኖቹ ታዛቢዎች ከተሰባሰቡ በኋላ ብቻ ይሁን፤ ቀድመህ ወደ ድምፅ የሚሰጥበት ክፍል አትግባ፤
- ከተወዳዳሪ እጩዎች ተወካዮች ጋር ጤናማ ግንኙነት ለመፍጠር ጥረት አድርግ፤

- ምርጫ ሳይጀመር ሁሉም ታዛቢዎች ባሉበት ኮሮጆው ባዶ መሆኑንና በተገቢና ግልፅ ቦታ መቀመጡን አረጋግጥ፤
- የሚስጢር ድምፅ መስጫው የግለሰቦችን የመምረጥ ነፃነትና ሚስጢራዊነት በሚያረጋግጥ ሁኔታ የተዘጋጀ መሆኑንና ሙሉ ቀንም በዚያው አኳኋን መቀጠሉን አረጋግጥ፤
- ምርጫው ሲጠናቀቅ ኮሮጆው በአግባቡ መታሸጉን አረጋግጥ፤
- ቆጠራ በትክክል እንዲካሄድ፣ የማንም ድምፅ ሳይቆጠር እንዳይቀር የበኩልህን ጥረት አድርግ፤
- የቆጠራውን ሂደት ሊያውክ የሚችል ማንኛውም ተግባር አትፈፅም፤
- አዝማሚያውን አይተህ ቆጠራው ሳይጠናቀቅ ቆጠራው እንዲታወክና እንዲቋረጥ ለማድረግ አትሞክር፤ የሚያውኩ ሲኖሩም ህጋዊ በሆነ መንገድ ቆጠራው እንዲካሄድ ታገል፤
- በቆጠራው ማረጋገጫ ቅጽ ላይ ውጤቱ በትክክል መሞላቱን አረጋግጠህ መፈረም አለብህ፤ ተገቢ ያልሆነ ስራ መሰራቱን ካረጋገጥህ አትፈርም፤
- ልዩነቶች ካሉህ አስመዝግብ ልዩነትህን በተጨባጭ መረጃ አስደግፈህ ለድርጅት የበላይ አመራርህ በእለቱ ሪፖርት አድርግ፤
- በህዝብ የተመረጡ ታዛቢዎች ከመጀመሪያው እስከመጨረሻው ከየትኛውም ተወዳዳሪ ደጋፊነት ገለልተኛ ሆነው እንዲታዘቡ የበኩልህን ጥረት አድርግ፤ ውግንና ሲያሳዩና አድልዎ ሲፈፅሙ በአግባቡ ታገል፤
- ከምርጫው አፈፃፀም መመሪያ ውጭ የሚፈፀሙ ተግባራትን በንቃት እየተከታተልክ በአግባቡ ታገል፤ በቸልታ አትለፍ፤ ሆኖም በረባ ባልረባው ሁሉ ክስ አታብዛ፣ በሂደቱ ላይ ከፍተኛ ተፅእኖ የሌላቸውና በቀላሉ መግባባት በሚቻልባቸው ጉዳዮች ሁሉ አትነዛነዝ፤

# ክፍል ሶስት

## የስነ-ምግባር ደንቡ በሚጥሱ ወገኖች ላይ ሊወሰዱ የሚገባቸው እርምጃዎች፣

### 1. መመሪያው የሚመለከታቸው ክፍሎች፣

- በየትኛውም ደረጃ ያለ የድርጅታችን አመራርና አባል ለመመሪያው ተፈፃሚነት በፅናት መስራት አለበት፤ ደንቡን የማክበርና የማስከበር ግዴታም አለበት።
- የድርጅታችን ደጋፊዎችም የስነ-ምግባር መመሪያውን አውቀው የማክበር ግዴታ አለባቸው።

## 2. መመሪያውን በሚጥሱ ወገኖች ላይ ሊወሰዱ የሚገባቸው እርምጃዎች፣

### ሀ/መመሪያውን የጣሰው አባል ከሆነ፣

- አባሉ በተገኝበት ስለተፈፀመው ስህተት ግምገማ እናካሂዳለን፤ በግምገማው መሰረት የተፈፀመው ስህተት ቀላልና ሊታረም የሚችል ከሆነ ማስጠንቀቂያ በመስጠት እናስተምረዋለን፡፡
- የተፈፀመው ስህተት መሰረታዊና ህገ-ወጥ ሆኖ ከተገኘ አባሉን በህገ-ደንባችን መሰረት ከድርጅታችን እስከማባረር ድረስ ርምጃ እንወስዳለን፡፡
- ጥፋቱ ወንጀል ከሆነ ግለሰቡ በፍትህ አካላት ተገቢው አስተዳደራዊና ህጋዊ እርምጃ እንዲወሰድበት ጥረት እናደርጋለን፡፡

### ለ/ መመሪያውን የጣሱት ደጋፊዎች ከሆኑ፣

- በቅድሚያ እየፈፀሙ ያሉት ተግባር ሕገ-ወጥ መሆኑን በመንገር ለማስተማር እንጥራለን፤
- የማይታረሙ ከሆኑ ይህን መሰል ተግባር የሚፈፅሙ ወገኖች ደጋፊዎቻችን እንዳልሆኑና ከኛ ጋር ምንም አይነት ግንኙነት እንደማይኖራቸው በይፋ እናጋልጣለን፤
- የተፈፀመው ተግባር ወንጀል ሆኖ ሲገኝ በተመሳሳይ ሁኔታ ለሕግ እንዲቀርቡና እንዲጠየቁ ለሚመለከተው አካል እናሳውቃለን፤ ሂደቱንም በባለቤትነት እንከታተላለን፤

## 3. በየደረጃው ያለ አመራር ሃላፊነትን በሚመለከት፤

- በየደረጃው ያለው አመራር በየትኛውም ደረጃ የሚፈፀሙ ስህተቶችን የመከታተልና የመቆጣጠር፣ ስህተቶች ከመፈፀማቸው በፊት የመከላከል ሃላፊነት አለበት፡፡
- ስህተቶች ተፈፅመው ሲገኙም ተጠያቂ የሆነው አካል ወይም ግለሰብ አግባብ ባለው የድርጅትና እንደክብደቱም በመንግስት ህግ እንዲጠየቅ የመወሰን፤ አፈፃፀሙንም የመከታተል ሃላፊነት አለበት፡፡
- የተፈፀሙ ስህተቶችን እያየ ወይም እያወቀ ተገቢውን እርምጃ ያልወሰደ አመራርም ጥፋቱን ከፈፀመው ግለሰብ ባልተለየ መንገድ ተጠያቂ ይሆናል፤ ተመጣጣኝ እርምጃም ይወሰድበታል፡፡